# ሆሣዕና

ከእንስሳት ተለይታ፣
ልትቀም በሰው ተርታ፤
ሊቀመጥባት ጌታዋ፣
ሊታወቅላት ዋጋዋ፣
ሳይጠፋባት አደራዋ፣
ሰው የማገልገል ሥራዋ፣
ሲመጣላት ፈጣሪዋ፣
ደስ አላት አህያዋ፣
ሲቀመጥባት በጀርባዋ።

ውርንጭላነቱ ቀርቶ፣
የታሰረችበት ገመድ ተፈትቶ፣
መናቅ መሰደቧ ጠፍቶ፣
የዋሁ የጽዮን ልጅ ትህትናን ተመልቶ፣
አስገባት ከተማ በሕዝቡ ፊት መርቶ።

አፋቸው ተለጉሞ፣
ሃሳባቸው ከፍቶ ጠሞ፤
አዋቂዎች ነን ባዮቹ፣
የአይሁድ ካህናት ግብዞቹ፤
ዝም ቢሉ ለምስጋና፣
ለመራቸው በደመና፣
ለመገባቸው ከሰማይ መና፣
መመስገኑ መች ቀረና፣
እየተባለ ሆሣዕና።

በሴቶች በወንዶቹ፣
በአዛውንት በልጆቹ፣
በሕጻናት ጡት ጠቢዎቹ።

የዘኬዎስ ምኞቱ፣
መቼ ተረሳ በእጥረቱ፣
ዛፍ ላይ ብቻ በመታየቱ፣
አልቀረም ፍላጎቱ፣
ለመዘመር መጓጓቱ፣
ገብቶለታል ወደ ቤቱ፣
የጽዮን ልጅ ያ ትሁቱ፣
ሊበላ አብሮት ከፍትፍቱ።

መቅደስ ገብቶ ዞሮ ሲቃኝ፣

ሲመለከት ጊዜ አባካኝ፣
ጸሎት ትቶ ሲቸረችር፣
ከሌባ ጋር ሲደራደር፣
አልቻለም ስለቤቱ፣
ሲያቃጥለው ቅንዐቱ፣
ጅራፍ ሠራ ለትምህርቱ፣
ቤቱን ሊያጠራ ከጠላቱ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ (መጋቢት 1996)
ለንደን